# በጥላቻ የተጋረደ ሐቅ

ከመኮንን አሻግሬ (ቨርጂኒያ አሜሪካ)

በዛሬ ጊዜ አንድ ከሚያደርገን ይልቅ እርስ በርስ የሚያናቁረንና ሊበታትነን የሚችል ንግግር፣ ጽሑፍና አካሄድ እየተስፋፋና ሥር እየሰደደ መጥቷል። ቁንጽል ታሪክ እየተመዘዘ፣ ከዚያም ዐልፎ ድርጊቱ ስለመፈጸሙ በታሪክ ያልተረጋገጠን ክስተት እዉነት አስመስሎ በማቅረብ ሕዝብ በሕዝብ ላይ እንዲነሣሣ ማድረግ የዘመኑ የፖለቲካ ፋሽን የሆነ ይመስላል። አንዳንድ ፖለቲከኞች ወይም ታሪክ ዐዋቂ ነን ባዮች "ነፍጠኛ" ብለዉ የሚጠሩት ሥርዓት ከመቶ አመት በፊት በኦሮሞ ብሔር ላይ አደረሰ ስለሚሉት በደል "እያንገሸገሻቸዉ" ሲናገሩ ስንሰማ ከማስደነቅ ዕልፎ በወቅቱ በአካል ተገኝተዉ በዐይናቸዉ ያዩ እስኪመስልን ድረስ ግራ አጋብተዉናል። ያንዳንዶቹም የጤና አይመስልም። እንደዉም አንድ ወቅት ያነበብኩት ሁልጊዜም ባስታወስኩት ቁጥር የሚገርመኝ ታሪክ አለ።

ጊዜዉ ወያኔ/ኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ ሥልጣን ከመያዙ በፊት ሚ/ር ኸርማን ኮህን የተባሉ አሜሪካዊ የለንደንን ኮንፈረንስ በሚመሩበት ወቅት የተከሰተ ነዉ። በወቅቱ ሥልጣን ላይ የነበረዉ የደርግ መንግሥትና ተቀዋሚዎች ተሳትፈዉ ነበር። ሚ/ር ኸርማን ኮህን ዉይይቱን ጤናማ ለማድረግና ይበልጥ ለማቀራረብ ከመፈለግ አንጻር እርስ በርስ እንዲጨባበጡ ይጠይቃሉ። ችግር አልነበረዉም። ሆኖም ግን ከኦነግ በኩል ተሳታፊ የነበረዉ አቶ አብዩ ገለታ የተባለ ግለሰብ አሻፈረኝ ይላል። ሚ/ር ኸርማን ኮህን ምክንያቱን ሲጠይቁትም "ከአማራ ጋር ደም ስለተቃባን አንጨባበጥም" በሚል ምላሽ ይሰጣል። በርግጥ ግለሰቡ እንደዚያ ተናግሮ ከሆነ በጣም የሚያሳፍርና የግለሰቡን አእምሮ ጤናማነት ጥያቄ ላይ የሚጥል ይሆናል።

በአጠቃላይ በብሔረሶቦች ላይ ምንም ዓይነት በደል አልተፈጸመም በሚል ክርክር ማቅረብ አይቻልም። አምባገነን ሥርዓት እስከነበረ ድረስ በደል መድረሱ አያጠያይቅም። ከሁሉም በላይ ግዛት ለማስፋፋትና ለማስገበር ሲባል ጦር ማዝመት የተለመደ ነበር። እንዳሁኑ ሰብአዊ መብት፣ ዲሞክራሲ … የሚሉ መርሖች ባለመኖራቸዉ በወቅቱ ተመሳሳይ እንቅስቃሴዎችን ለመግታትም ሆነ ለማዉገዝ አይቻልም ነበር። በዚህም መሠረት ጉልበት ያለዉ ያሰኘዉን የሚያደርግበት ጊዜ ነበር። ሆኖም ግን ለምን የአጼ ምኒልክ ገንኖ እንደወጣ አይገባኝም። በርግጥ ያንን ሁሉ በደል አድርሰዋል? የእሳቸዉ ግዛት ማስፋፋት ወይም ማስገበር ያነጣጠረዉ በኦሮሞ ብሔር ላይ ብቻ ነበር? በሌሎች አካባቢዎች ወይም ብሔረሰቦች ላይ ተመሳሳይ ጥቃት አልተፈጸመም፣ የሌላ ብሔር አባል የሆኑ ገዥዎችስ ተመሳሳይ በደል በሌላዉ ሕዝብ ላይ አልፈጸሙም … የሚሉት ጥያቄዎች በጥንቃቄ መታየት ያለባቸዉ ይመስለኛል።

"ከአሜን ባሻገር" በሚል ርዕስ በቅርቡ በዕዉቀቱ ሥዩም ያሳተመዉ መጽሐፍ ለእነዚህና ለሌሎችም በተለምዶ በአጼ ምኒሊክ ላይ ሲላከከባቸዉ ለነበሩት ክሶች በቂ ምላሽ እንደሚሰጥ አምናለሁ። መጽሐፉ የዉጭና የአገር ዉስጥ ጸሐፊያንን በማጣቀስ የተጻፈ በመሆኑ ተቃራኒ ማስረጃ እስካልቀረበ ድረስ ተዓማኒነቱ አያጠራጥርም። በዚህም ደራሲዉ ሊደነቅና ሊመሰገን ይገባዋል።

በዕዉቀቱ ሥዩምን በሥነ ጽሑፍ ሥራዎቹ የማያዉቀዉ ኢትዮጵያዊ ያለ አይመስለኝም። በቁም ነገር የታጀቡት ለዛ ያላቸዉ መነባንቦቹ እጅጉን ይመስጡኛል። "ከአሜን ባሻገር" የሚለዉ መጽሐፉ ግን ከሥነ ጽሑፍነት በላይ የገዘፈ ትልቅ ምርምር የሚጠይቅና ግራ ቀኙን ያገናዘበ ሚዛናዊ ጽሑፍ ለመሆኑ መጽሐፉን ያነበበ ሁሉ ሊመሰክር ይችላል። "ዉሸት ሲደጋገም እዉነት ይሆናል" እንዲሉ በመንግሥትና በሌሎችም የግል ሚዲያ ሆን ተብሎ በሚነገሩና በሚጻፉ ስም ማጥፋትና ታሪካችንን ጥላሸት የመቀባት ሰለባ ለሆኑ ሰዎችም ቆም ብለዉ እንዲያስቡና ከጅምላ ፍረጃ እንዲታቀቡ የሚያድርግ መጽሐፍ እንደሆነ አምናለሁ።

እነዚህ ታሪካችንን ጥላሸት በመቀባትና አንዱን ብሔር በሌላዉ ላይ ለማነሣሣት የተጠመዱ ሰዎች ከዚያ ጀርባ የሚያገኙት የፖለቲካ ትርፍ በመኖሩ እንጂ በእዉነት እንደሚባለዉ ያህል አጼ ምኒሊክ በኦሮሞ ሕዝብ ላይ በደል አድርሰዉ ቢሆን እንኳን ከመቶ ዓመት በኋላ መነጋገሪያና ለትግል የሚያነሣሣ ሆኖ ባልቀረበ ነበረ። በተለይም የግፍ ዕዳ ተሸካሚ የሆነ ይመስል የአማራ ሕዝብ ሆን ተብሎ የጥቃቱ ሰለባ ባልሆነ ነበር። እዚህ ላይ የበደኖን፣ የአርባጉጉንና የሌሎችንም ዕልቂት መጥቀስ ይቻላል።

በአንድ ወቅት የቅኝ ግዛት መስፋፋትን ተከትሎ በአፍሪካ፣ በላቲን አሜሪካና በሌሎች አገራት ላይ አዉሮፓዉያን ከፍተኛ ዕልቂት መፈጸማቸዉ የሚካድ አይደለም። ሀብታቸዉ ተዘርፏል። በገዛ አገራቸዉ ላይ አንገታቸዉን ደፍተዉ እንዲኖሩ ተገደዋል። ከዚያም በላይ በርካታ ኢሰብአዊ ድርጊት ተፈጽሞባቸዋል። ኢትዮጵያም ቢሆን በጣልያን ለሦስት ጊዜ ያህል የጥቃት ሰለባ ሆና ነበር። ሆኖም ግን በጀግኖች አባቶቻችን ተጋድሎ በቅኝ ግዛት ሥር ሳንወድቅ ቀረን። ያም ቢሆን በወረራዉ ሳቢያ በርካታ ሰዎቻ አልቀዉብናል። ንብረትም ወድሟል። እንደዚያም ሆኖ ኢትዮጵያን ጨምሮ ማናቸዉም የቀድሞ ቅኝ ግዛት አገራት በሰላም አርፈዉ ከተቀመጡበት መጥተዉ በወረሯቸዉ የአዉሮፓ አገራት ላይ የጥላቻ ፕሮፓጋንዳ ሲሠሩና

በበቀል ተነሣሥተዉ ጉዳት ሲያደርሱባቸዉ አይስተዋልም። እንደዉም በመንግሥታት መካከል መልካም ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ጎልብቶ ይታያል። ሕዝቡም ቢሆን በመልካም ፈቃደኝነት የሚሰደድባቸዉ አገራት ሆነዋል።

ናዚ ጀርመን በይሁዶች ላይ ያደረሰዉን ያክል ዕልቂት በማንም ሕዝብ ላይ ደርሶ የሚያዉቅ አይመስለኝም። ከስድስት ሚሊዮን በላይ አይሁዶች በግፍ እንደተገደሉ ይታመናል። በርካቶችም ወደተለያየ አገራት ለመሰደድ ተዳርገዋል። የሁለተኛዉ አለም ጦርነት በጀርመን ሽንፈት ከተደመመ በኋላ ናዚዎች በተለይም በአይሁድ ሕዝብ ላይ ያደረሱትን በደል የሚዳኝ እንደኑሪምበርግ ትሪያልስ (Nuremberg Trials) ያሉ የዳኝነት አካል በማቋቋም ጉዳያቸዉ ታይቶ ዉሳኔ ተሰጥቶባቸዋል። ከዚያ በኋላ ጀርመንና እስራኤል እ.ኤ.አ. በ1965 ዓ.ም. በይፋ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ጀምረዋል። በርግጥ መጀመሪያ አካባቢ በእስራኤሎች ዘንድ ጀርመኖችን ያለማመን ሁኔታ ይታይ ነበር። እያደር ግን ግንኙነታቸዉ እየተጠናከረ መምጣት ቻለ። በአሁኑ ሰዓት ከአሜሪካ ቀጥሎ ጀርመን ለእስራኤል ከፍተኛ የንግድ አጋር ስትሆን አዉሮፓ ካሉ አገራት መካከል ግን ትልቁን ድርሻ የምትይዘዉ ጀርመን ነች። መጠነ ሰፊ የሆነ የሳይንስ ግንኙነትም አላቸዉ። በየዓመቱ በሺህ በሚቆጠሩ ወጣት ጀርመኖችና እስራኤሎች መካከል የሥራ ልዉዉጥ ይደርጋል። እንዲሁም እ.ኤ.አ. ከ1961 ጀምሮ ወደ 2,500 የሚሆኑ ጀርመናዊ በጎ ፈቃደኞች በእስራኤል ሆስፒታል እና የማኅበራዊ ዌልፌር ፕሮግራም (Social Wefare Programs) ዉስጥ አገልግለዋል። ዝርዝሩ ብዙ ነዉ። ዋናዉ ነጥብ ዓላማዉ ላይ ነዉ።

ዓላማዉ ቀደም ሲል አይሁዶች የሚሰቀጥጥ በደል ስለደረሰባቸዉ ያንን ጉዳት ለማካካስ፣ የሁለቱ አገራት ሕዝብ መካከል የሻከረ ግንኙነት እንዳይኖር እንደዉም ከዚያም በላይ ጥሩ የወዳጅነትና የአጋርነት መንፈስ እንዲሰርጽ ለማድረግ ነዉ። የሚፈለገዉም ይህ ነዉ። አንድ ጊዜ የተፈጸመን ድርጊት/በደል ወደኋላ ተመልሶ ማስተካከል ወይም እንዳይሆን ማድረግ ስለማይቻል የድሮዉን እያነሡ አፍራሽ የሆነ አካሄድ መከተልና ከዚያም በላይ ጥላቻ መዝራት ለሁለቱም ወገን ጠቃሚ እንዳልሆነ ገብቷቸዋል።

ጃፓን እ.ኤ.አ. ታህሳስ 7 ቀን 1941 ዓ.ም. የአሜሪካንን ፐርል ሃርበር (Navala base at Pearl Harbor) ደብድባለች። በድብደባዉም 2,300 አሜሪካኖች አልቀዋል። እንዲሁም ተዋጊ መርከቦች ወድመዋል። አሜሪካንም በብቀላ መልክ ሂሮሽማና ናጋሳኪ በተባሉ የጃፓን ግዛቶች ላይ አቶሚክ ቦምብ ጥላለች። በዚህም በሂሮሽማ ብቻ ከ80,000 እስከ 140,000 ሰዎች ሲያልቁ ከ100,000 ሰዎች በላይ ከባድ የመቁሰል አደጋ ደርሷል። በፍንዳታዉ ከሁለት ሦስተኛ በላይ የሚሆኑት የሂሮሽማ ሕንፃዎች ወድመዋል። እንዲሁም ከፍንዳታዉ ከሠላሳ ደቂቃ በኋላ በስተሰሜን ምዕራብ አቅጣጫ ከባድ ዝናብ ዘንቦ ነበር። ይህ ጥቁር ዝናብ “black rain” በመባል የሚታወቀዉ ዝናብ ከቆሻሻነቱ ባሻገር በፍንዳታዉ ምክንያት አየር ላይ ስፍፎ የነበረዉን ሬዲዮ አክቲቭ ንጥረ ነገር “radio active” የያዘ ነበር። ይህም ከፍንዳታዉ በጣም ሩቅ የሆኑ አካባቢዎችንም ጭምር ሊበክል ችሏል። እንዲሁም በናጋሳኪ ላይ ያዘነበችዉ ቦምብ የከተማዋን 40% አዉድሞታል። ፍንዳታዉን ተከትሎ ለአመታት ያህል ባልተለመደ መልኩ ከፍተኛ ካንሰር፣ ጉድለት ያላቸዉ ልጆች መዉለድ፣ የቱመር ችግርና ሌሎችም ዓይነት የጤና ችግሮች ተከስተዋል። ከፍንዳታዉ የተረፉትም ሰዎች ለከፍተኛ የሥነ ልቦና ጉዳት ተዳርገዉ ነበር። በአሁኑ ጊዜ ግን በሁለቱ መንግሥታትም ሆነ ሕዝቦች መካከል የጥላቻ ፕሮፓጋንዳ ሲነዛ አይታይም። እንደዉም ፍጹም ሊባል የሚችል ሰላማዊ ግንኙነት አላቸዉ።

ይህንን ጽሁፍ ለማንበብ ዕድል ያገኘ ሁሉ ሩዋንዳ ላይ ዕልቂት ሲፈጸም በዜና ማሰራጫዎች አማካኘት ለመስማት ያልታደለ ሰዉ ይኖራል የሚል ግምት የለኝም። እ.ኤ.አ. በ1994 ዓ.ም. 85% የሆኑት የሁቱ ጎሣ አባላት 14% የሆኑትን የቱሲ አባላት በሦስት ወራት ጊዜ ዉስጥ 800 ሰዎችን በቆንጨራ ለመፍጀት በቅተዋል። አፈጻጸሙ ለዚህ ዘመን የማይመጥንና ፍጹም ጭካኔ የተሞላበት ስለመሆኑ “Hotel Rwanda” እና “Sometimes in April” የተሰኙ ፊልሞችን የተመለከተ ሁሉ የሚያረጋግጠዉ ሐቅ ነዉ። የሆነዉ ሆኖ ይህንን ጉዳይ እንዲያይ በተቋቋመዉ ፍርድ ቤት አማካኝነት በአጥፊዎቹ ላይ ፍርድ ከተሰጠ በኋላ የመንግሥት ቀሪ ሥራ ትናትና የተፈጸመዉን በማንሣት በሁለቱ ጎሣዎች ጥላቻን መዝራትና በተለይም ቱሲዎችን ለበቀል እንዲነሣሡ ማድረግ አልነበረም። ፕሬዚዳንት ፖል ካጋሜ የቱሲ ጎሣ አባል ቢሆኑም ያንን ባለማድረጋቸዉ ከእኛ አገር መሪዎች ጋር ሲነጻጸሩ ሊደነቁ ይገባል። እንደዉም ዕዉቅና ያገኙት በሰላም ግንባታ፣ ዕርቅ፣ የልማት እንቅስቃሴ፣ የሰብአዊ መብት ጥበቃን ማሻሻል፣ ሴቶች ለሥልጣን ለማብቃት በሚያደርጉትና በሌሎች እንቅስቃሴዎች ነዉ። ኢኮኖሚያቸዉም ዕድገት እያሳየ ነዉ። እንዲሁም ሁሉም ጎሣ አባላት ሩዋንዳዊ ስለመሆናቸዉ እንጂ ራሳቸዉን በጎሣ እንዳገልጹ ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል። በርግጥ ለብዙ ዓመታት የኖረ በመሆኑ በአንድ ጊዜ በቀላሉ ማጥፋት ከባድ ቢሆንም መሻሻሎች እየታዩ ነዉ።

በርካታ ምሳሌዎችን ማንሣት ይቻላል። ሆኖም ግን ለአብነት ያህል በቂ ይመስለኛል። ታዲያ የኢትዮጵያ ሁኔታ ለምን ከሌላዉ ዓለም ይለያል? ለምንድን ነዉ ምኒሊክ ከመቶ ዓመት በፊት በኦሮሞ ሕዝብ ላይ ያደረሱት “በደል/ጥፋት” በሚል ዘወትር የሚደሰኮረዉ? የአማራ ሕዝብስ በምን ሒሳብ ነዉ አጼ ምኒሊክ ፈጸሙ ለሚባለዉ “በደል” ተወቃሽና ከዚያም በላይ ፕሮፖጋንዳዉ በሚፈጥረዉ ጥላቻ ሳቢያ ሰለባ የሚሆነዉ? ደግሞስ ማነዉ አጼ ምኒሊክን የአማራዉ ሕዝብ ወኪል ያደረጋቸዉ?

አንድ ወቅት እንደዚህ ዓይነት ድርጊት ተከስቶ ነበር የሚለዉን ከማስተጋባት ባሻገር ያሁኑ ትዉልድ ወራሽ ሊሆንበት የሚችልበት አንዳችም ምክንያት አይታየኝም። እንደዚያማ ቢሆን ኖሮ አጼ ዮሐንስን ጨምሮ በዘመኑ ከትግራይ አካባቢ

የተነሱ መሪዎች ግዛታቸዉን ወይም ክርስትናን ለማስፋፋት ወይም በሌላም ምክንያት በሌላዉ ብሔረሰብ ላይ ላደረሱት ጭፍጨፋ አሁን ያለዉ የትግራይ ሕዝብ ወይም መሪዎቹ የተነሱበት ብሔር ወራሽ ሆነዉ ተጠያቂ ሊሆኑ በተገባ ነበር።

ሥልጣን ላይ ያለዉ ወያኔ/ኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ. መንግሥት ኃላፊነት የማይሰማዉና ሆን ብሎ ሕዝብን በሕዝብ ላይ የሚያነሣሣ አካሄድ መከተሉ በግልጽ የሚታይ ነዉ። አለመታደል ሆኖ እንደመንግሥት በአገሪቷ ላይ ሰላም እንዲሰፍን፣ በሕዝብ መካከል ጥርጣሬ እንዳይኖር፣ የትብብር መንፈስ እንዲጎለብት ... ወዘተ ማድረግ ሲገባዉ አፍራሽ በሆነ መልኩ በመንቀሳቀሱ ዛሬ ያለንበት ደረጃ ላይ ለመድረስ በቅተናል። ከመቶ ዓመት በፊት ተፈጸመ ለሚባለዉ "ጡት ቆረጣ" ስለመፈጸሙ እንኳን ከታሪክ ድርሳናት ለማረጋገጥ ሙከራ ሳያደርግ በሃያ ሚሊዮን ብር "አኖሌ የጡት ቆረጣ" የሚል ሐዉልት ማቆሙም የሚያሳፍር ነዉ።

የመንግሥት ሳያንስ አንዳንድ ግለሰቦችም ይህንኑ ሥራዬ ብለዉ አጼ ምኒሊክ አርሲ ላይ በኦሮሞ ሕዝብ ላይ ያደረሱት አሰቃቂ ጭፍጨፋ፣ የኦሮሞ ሕዝብ በማንነቱና በባሕሉ እንዳይኮራ በነፍጠኛዉ/በአማራዉ ሕዝብ የደረሰበት ወይም እየደረሰበት ያለዉ በደል ... ወዘተ በሚል የጥላቻ ዘር ይዘራሉ። ሁላችንም ቢሆን እንኳንስ በኦሮሞ ወገናችን ላይ ቀርቶ በማንም ሰብአዊ ፍጡር ላይ ጭፍጨፋ ሲደርስ እናዝናለን። እነሱ ግን ለአሮሞ ሕዝብ ተቆርቁረዉ አይደለም። ዋናዉ ዓላማቸዉ የኦሮሞ ሕዝብና የአማራዉ ሕዝብ እንዲቃቃር ማድረግ ነዉ። ከዚያም በላይ የኦሮሞ ሕዝብ ለበቀል እንዲነሣሣና አማራዉን ወደ መጨፍጨፍ እንዲሄድ የሚገፋፋ አካሄድም ይመስላል። ሆኖም ግን እነሱ በጣሩት መጠን በሕዝቦች መካከል መጨፋጨፍ አልተከሰተም። በርግጥ በሚነዛዉ መርዛማ ፕሮፖጋንዳ ተለክፈዉ መለያየት ወይም መቃቃር ደረጃ የደረሱ ሰዎች መኖራቸዉ አይካድም። በአብዛኛዉ ግን በጋብቻ፣ በጓደኝነትና አብሮ በመኖር ለዘመናት የዘለቁ በመሆናቸዉ አሁንም ፍቅሩ እንዳለ ነዉ። እኔ ራሴ ካሉኝ ጓደኞች ዉስጥ በጣም የምወዳቸዉ ሁለት የኦሮሞ ብሔር ይገኙበታል። በየጊዜዉ በስልክ አገኛቸዋለሁ። ምናልባት ኢትዮጵያ ብሄድ ላገኛቸዉ ከምጓጓዉ ወዳጆቼ መካከል አምስት ሰዎች ብቻ ምረጥ ብባል እነዚህን ሁለት ኦሮሞ ጓደኞቼን ማካተቴ አይቀርም ነበር።

ከእነዚህ ጥላቻን ከሚነዙት ግለሰቦች መካከል ጋዜጠኛና ደራሲ ተስፋዬ ገብረአብ ይገኝበታል። ይህ ግለሰብ ደብረ ዘይት (ቢሾፍቱ) ተወልዶ ያደገ ነዉ። በትዉልድ ግን ኤርትራዊ ነዉ። በአንድ ወቅት የኢትዮጵያ ፕሬስ መምሪያ ኃላፊ ነበር። ሌሎች ኃላፊነቶችም ነበሩት። ጥሩ የመጻፍ ችሎታ አለዉ። ሆኖም ግን በቂ የታሪክ ዕዉቀት ያለዉ አይመስልም። በሥነ ጽሑፎቹ ዉስጥ አርሲ ላይ የኦሮሞ ሕዝብ በአጼ ምኒሊክ አሰቃቂ ዕልቂት እንደተፈጸመባቸዉ፣ ኦሮሞ ለም መሬቱን በነፍጠኛ/በአማራ እንደተነጠቀ፣ ኦሮሞ ተወላጆች በስማቸዉ በማፈር ስማቸዉን ለመቀየር መገደዳቸዉን፣ ኦሮሞዎች በማንነታቸዉ እንዲያፍሩና በባሕላቸዉ እንዲሸማቀቁ እንደሚደረጉ ... ወዘተ በመስበክ ይታወቃል። ይህንንም ለማሳየት የጻፋቸዉን ጽሑፎችና ያደረጋቸዉን ቃለመጠይቆች ማጤን ተገቢ ነዉ። ከዚያ በፊት ግን ይህ ሰዉ እንደሚለዉ በኦሮሞ ብሔረሰብ መካከል ስላደገ ለእነሱ ካለዉ ፍቅር የመነጨ ነወይ የሚለዉን ጥያቄ መመለስ ያስፈጋል። አይመስለኝም። የሚወድ ሰዉ ጥላቻን አይዘራም። ጥላቻ መርዝ ነዉ። ከነቀርሳ የከፋ ጉዳት ያስከትላል። አስተሳሰብን ያዛባል። ለክፋትም ይዳርጋል። ፍቅር ግን ምኅረትን ያወርዳል። በማኅበራዊ እንቅስቃሴም ሰላምንና መቻቻልን ያሰፍናል። ስለሆነም የሚወድ ሰዉ ፍቅርን፣ ይቅርባይነትንና መቻቻልን መስበክ ቀዳሚ ዓላማዉ ያደርጋል እንጂ በአሉታዊ መልኩ አይንቀሳቀስም።

ተስፋዬ ገብረአብ ይህንን የሚያደርግበት የራሱ ዓላማ ያለዉ ይመስለኛል። የቀድሞዉ ዳኛ አቶ ወልደሚካኤል መሸሻ "ጊዜ መስተዋቱ! ተስፋዬ ገ/አብ ማነዉ" በሚል ርዕስ በኢትዮጵያ ሚዲያ ላይ ሰፊ ዘገባ አቅርበዉ ነበር። በራሱ በተስፋዬ እጅ ጽሑፍ የተጻፉ በርካታ ሰነዶችም ቀርበዋል። ዋናዉ ነጥብ ጽሑፉም ሆነ ሰነዶቹ የሚያመላክቱት ተስፋዬ ገብረአብ ተራ ጸሐፊ ሳይሆን ከኤርትራ ደኅንነት ጋር በቅርበት የሚሠራ ግለሰብ እንደሆነ ነዉ። የሚጽፈዉም እየታዘዘና እነሱን እያማከረ ከዚያም በላይ የገንዘብ ድጋፍ እየተደረገለት እንደሆነ መረዳት ይቻላል። ታዲያ ከእንደዚህ ዓይነት ሰዉ ምን ልንጠብቅ እንችላለን? ለምንስ አንዳንድ ሰዎች ይህ ሰዉ በሚነዛዉ ፕሮፖጋንዳ ሰለባ ሆኑ? ለማንኛዉም እስኪ ወደጽሑፎቹ እንመለስ፡-

## 1) <u>የቡርቃ ዝምታ</u>

ይህ መጽሐፍ ታሪካዊ ልብ ወለድ በሚል በ1992 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ከተማ ነዉ የታተመዉ። በአወዛጋቢነቱ ግንባር ቀደም ሆኖ ሊጠቀስ ይችላል። በመሠረቱ ይህ መጽሐፍ በምንም መስፈርት "ታሪካዊ ልብወለድ" ሊባል አይችልም። ሲጀመር መነሻ ያደረገዉ በጽሑፍ የተደገፈ ታሪክን ሳይሆን ፖለቲከኞች ከበስተጀርባ የራሳቸዉን አጀንዳ ለማስፈጸም ሲሉ አንድን ሕዝብ በሌላዉ ላይ ለማነሣሣት የሚነዙትን ፕሮፖጋንዳ ነዉ። ታሪክን በቁንጽል በመዉሰድ፣ እዉነታዉን በማጋነንና አንዱን ወገን እጅግ ጨካኝ ብሎም ታይቶና ተሰምቶ የማይታወቅ ድርጊት እንደፈጸመ ለማስመሰል በተጓዳኝ የፈጠራ ትረካዎች የተገነባ መጽሐፍ ነዉ።

"ታሪካዊ ወይም ታሪክ ቀመስ ልብወለዶች" ለአገራችን ሥነ ጽሑፍ አዲስ አይደሉም። ኢትዮጵያዊ ጀግንነት፣ አይበገሬነት፣ ላገሩ የነበረዉን ፍቅር የገለጸበትን ተጋድሎ የሚተርኩ በልብ ወለድ መልክ የተጻፉ እንዲሁም ከጊዜዉ የቀደመ ላገራቸዉ ትልቅ ራእይ ስለነበራቸዉ ስለአጼ ቴዎድሮስ በልብ ወለድ መልክ የሚተርኩ እንደ ታንጉት ሚስጥር (በብርሃኑ ዘሪሁን)፣ አንድ ለእናቱ (በአቤ ጉበኛ) … ወዘተ መጥቀስ ይቻላል። ሆኖም ግን እነዚህን ልብ ወለዶች አንብበን ከሚሰማን የአገር ፍቅር፣ የአገር ኩራት፣ ወኔ ... አንጻር የተስፋዬን "የቡርቃ ዝምታ" ስንመዝነዉ ጥላቻን የሚዘራ፣ አለመተማመንን የሚፈጥር፣ ለቁጭት የሚዳርግ

እንዲሁም ከሌሎች መሰል መርዘኛ ንግግሮችና ጽሑፎች ጋር ተዳብሎ አንዱን ብሔር በሌላዉ ላይ ለማነሣሣት ጉልበት ያለዉ ሆኖ እናገኘዋለን።

## 2) ጫልቱ እንደሄለን

ተስፋዬ ገብረአብ የደራሲዉ ማስታወሻ የሚለዉ መጽሐፉ ላይ ጫልቱ እንደሄለን የሚል ትረካ ከገጽ 66 - 100 ድረስ አቅርቦልናል። አዉቶብስ ዉስጥ በመጓዝ ላይ እያለ አንድ ግለሰብ ያጫወተዉን ታሪክ ተመርኩዞ እንደጻፈዉ ገልጿል። በተጨማሪም " ... እዉነተኛ ቢሆንም የደራሲ ብዕሬን በመጠቀም ምናባዊ ገጸ ባሕሪያት ጨምሬበታለሁ" በማለት አስፍሯል። ለማንኛዉም የታሪኩ ዋና ፍሬ ነገር እንደሚከተለዉ ነዉ።

ጫልቱ በትዉልድ አካባቢዋ የቱለማ ታሪክ ላይ ከወንዶች ጋር ተወዳድራ በማሸነፏ ፈረስ በመሸለሟ ዝነኛ ነበረች። በዚያ ላይ ቆንጆና ፈረስ ጋላቢ በመሆኗ ዝናዋ ሊገን ችሏል። በአስራ አምስት አመቷ ብትዳርም ኮብልላ አዲስ አበባ ከአክስቷ ጋር መኖር ጀመረች። አማርኛ መስማትና መናገር ካልቻለች ትምህርት ቤት ልትገባ እንደማትችል አክስቷ ስለነገረቻት ከመጀመሪያዉ ቀን ጀምሮ አማርኛ መማር እንደጀመረች ተጠቅሷል። እንዲሁም አማርኛ ፈጥና ለመልመድ ኦሮምኛ መናገርና ማቆም እንደሚገባም አሳስባታለች። በመቀጠልም ጫልቱ ሚደቅሳ የተባለዉ ስም ከቁመናዋና ከቁንጅናዋ የማይስማማ በመሆኑ ስሟን ከነአባቷ ስም መቀየር እንደሚገባ ነግራት ሄለን ጌታቸዉ (ጌታቸዉ የአክስቷ ባለቤት ስም መሆኑ ነዉ) ተብላ ልትጠራ በቅታለች። እንደዉም ቃል በቃል አክስቷ ያለቻት " ... ይህንን መልክና ቁመና ይዘሽ ጫልቱ ተብለሽ መጠራት ይጎዳሻል። ንቅሳት ባያደርጉብሽ ጥሩ ነበር። ግን አንድ ጊዜ ሆኗል። ምንም ማድረግ አይቻልም። አባትሽ መልክሽን አበላሽቶታል። ይህንን የመሰለ ዉበት እንዲህ ማበላሸት በጣም ያሳዝናል። ቢሆንም ግን አማርኛሽን ካስተካከልሽ ምንም አይደለም ... " (ገጽ 73 ይመለከቷል።) ይህም በመሆኑ ሄለን ስትወደስበትና ስትኮራብት የነበረዉ ስም ከነአባቷ ስም ጭምር በመቀየሩ እንዲሁም የዉበት መለኪያ የሆነዉ ንቅሳት በመንቋሸሹ ግራ እንደገባትና አእምሮዋን እንደረበሻት ተገልጿል።

ብሩሕ አእምሮ አላት ተብሎ ስለተገመተና የአማርኛ ቋንቋዋም ስለተሻሻለ ትምህርት ቤት እንድትገባ ተወሰነ። ሆኖም ግን ኑሮ ዐልጋ በዐልጋ እንዳልሆነላት ተገልጿል። ለምሳሌ አንድ ጊዜ የአቴቴን መዝሙር ስታዜም የሰሙት የአክስቷ ልጆች እናታቸዉ ፊት ደግመዉት ነበር። ያኔ የአክስቷ ዐይኖች በድንጋጤ ፈጠዉ "ጥንቆላ ታስተምሪያቸዉ ጀምር?" በማለት እንዳባረቀችባት በገጽ 76 ላይ ተተርኳል። በተጨማሪም የአክስቷ ባል ጣልቃ ገብቶ ስለትርጉሙና ቤተ ክርስትያን ዉስጥስ ምን ብለዉ እንደሚዘምሩ ለጠየቃት ጥያቄ የሰጠችዉን መልስ በመመርኮዝ " ... እኛ ክርስቲያኖች ነን። አንቺም ክርስቲያን ነሽ። ቃልቻ፣ ጨሌ የሚሉት የሰይጣን ልማድ ነዉ። ሰይጣን እንዲህ ያለ ቀዳዳ እየፈለገ ገብቶ ንጹህ መንፈሳችንን ያቆሸሻል ... ላንቺም ለሁላችንም የቃልቻዉን ጸሎት ከግቢያችን ማራቅ ይሻላል ... " ብሏታል (ገጽ 76 እና 77 ይመለከቷል።) ሌላ ጊዜ ደግሞ ለምን "የዋሬና ኦኮሌ ሥርዓት እንደማይደርግ ስትጠይቅ " ... ቆፍቱ ሳለሽ የምታዉቂዉን ሁሉ እንደሌለ እርሽዉ ... እዚህ እሬቻ አናደርግም። ዋሬ የለም! ኦኮሌ የለም። ኢብሳ ኦሮሞ የለም። አቴቴ የለም .... " በማለት አክስቷ በቁጣ መልሳላታለች (ገጽ 78 ይመለከቷል።) በመሆኑም እነዚህ በምስጋና መልክ የሚቀርቡ የከበሩ በዓላትና ስታደንቃቸዉ የነበሩ "የአስተሳሰቧ ወንች" አዲስ አበባ ዉስጥ ተንቋሸዉና ነዉር ሆነዉ በመገኘታቸዉ ፍርኅት እንደለቀቀባት ተጠቅሷል።

ትምህርት ቤት ስትገባ ደግሞ ሁሉም ሰዎች የተመካከሩ ይመስል " ... ቆንጆ ነበርሽ! የሆንሽ ንቂሳ ጋ_ ሆንሽ እንጂ ... ይህን የመሰለ ዉበት ቸክችከዉ አበላሹት ... " ስለሚሏት ገንብታዉ ከኖረችዉ ኩራት ጋር ፍጹም እየተጋጨና መንፈሷን እንዳናወጠዉ ገጽ 80 ላይ ተጠቅሷል። በሌላ በኩል ደግሞ አቶ ጽጌ የሚባሉ የእንግሊዘኛ መምህር ተማሪዎች በሄለን ላይ በቋንቋዋና በንቅሳቷ እንዳይስቁባት እንዲሁም ሁለት ቋንቋ በመናገሯና በትምህርቷም ጎበዝ በመሆኗ ከሁሉም እንደምትበልጥ በመመስከር "የሚያንቋሽሿትን ተማሪዎች" እንደገሰጿቸዉ ገጽ 87 እና 88 ላይ እናገኛለን።

በዚህ ዓይነት ሁኔታ አዲስ አበባ ዉስጥ ቆይታ አንድ ወቅት ወላጆቿን ለመጠየቅ ወደ ቆፍቱ ሄደች። ከመሄዷ በፊት ግን አክስቷ " ... ኦሮምኛ ካወራሽ አማርኛሽ ድርግም ብሎ ነዉ የሚጠፋብሽ። ስለዚህ 'ኦሮምኛ ረሳሁ' ብለሽ በአማርኛ ብቻ አዋሪያቸዉ። ከእናትሽ ጋር ሳይቀር በአማርኛ አዉሪ። ጫልቱ የሚለዉን ደግሞ መልሰዉ እንዳያስለምዱሽ ሄለን መሆንሽን ንገሪያቸዉ። ጫልቱ ብለዉ ቢጠሩሽ መልስ አትስጪ ... " በማለት እንደመከረቻት ገጽ 90 ላይ ተወስቷል። በዚህም የተነሣ ገበያ መዉጣት ችግር እንደሆነባትና ዘመድ ለመጠየቅ በየመንደሩ ስትሄድ ስሟን በመለወጧ ጥያቄ እንደሚቀርብላትና በአማርኛ ብቻ መልስ በመስጠቷ እንደዚያ በነገሰችበት መንደር ትርፉ መናቅን እንዳተረፈላትና 'አባቷ ሸገር ልኮ ገደላት። ያችን የመሰለች ልጅ እንዲህ ሆና ቀረች' በሚል ሊዘበትባት እንደበቃ ገጽ 96 እና 97 ላይ እናገኘዋለን።

ከዕረፍት ቆይታዋ ብትመለስም ወደ አዲስ አበባ እንዳልተመለሰችና እንደዉም ባል አግብታ ለመኖር እንደሞከረች ሆኖም ግን ባሏ በመሞቱ እንደተቸገረች መጽሐፉ ያትታል። በማንነት ላይ የተፈጠረባት ዉዥንብር ግን የደርግ ሥርዓት ወድቆ ኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ "የነፍጠኛ ሥርዓት በብሔር ብሔረሰቦች ላይ ያደረሰዉ በደል" በሚል በከፍተኛ ደረጃ በሚስተጋባት ጊዜም በማንነቷ ላይ የተፈጠረባት ዉዥንብር እንደቀጠለ መጽሐፉ ይተርካል። በመሆኑም ሄለንነቷ በኖ ቢጠፋም ወደ ጫልቱነቷ በቀላሉ መመለስ ባለመቻሏ ምን መሆን እንዳለባት ግራ ተጋብታ እንደነበር በመጨረሻም በ1994 ዓ.ም. ወደ ቆፍቱ በመመለስ እናቷን ይቅርታ ስለመጠየቋ ተወስቷል (ገጽ 99 ይመለከቷል።)

ወዳደገችበት ቀየ ብትመለስም ሕይወት ለጫልቱ ጥሩ እንዳልነበረ ተጽፏል። ብቸኛ ሆና እንደሰነበተች፣ ከእናቷ በስተቀር ማንንም ለማነጋገር ፈቃደኛ እንዳልነበረች፣ እያደርም ምግብ መዉሰድ እንደቀነሰች፣ ወደገበያ መሄድ ጨርሶ እንዳቆመችና በአጠቃላይ ከቤት መዉጣት እንደማትፈልግ ደራሲዉ ለመግለጽ ከሞከረ በኋላ በስተመጨረሻ አንድ ቅዳሜ ቀን ቡና ጠጥታ ጋደም እንዳለች በዚያዉ እንዳሸለበች ጽሁፉ ይደመድማል። የመሞቷ ምክንያትም አከራካሪ ሊሆን እንደሚችል መግቢያዉ ላይ ተገልጿል። ምናልባትም በደረሰባት "በደል" በሁኔታዎች በመገፋፋት ራሷን ያጠፋች (መርዝ ጠጥታ ሊሆን ይችላል) እንዲመስል ጽሑፉ የሚገፋፋ መንፈስ አለዉ።

ታሪኩ ዕዉነት ነዉ ወይስ ሙሉ ለሙሉ የፈጠራ ነዉ የሚለዉን ለጊዜዉ ወደ ጎን ትተን ለማስተላለፍ የተፈለገዉ መልዕክት ላይ ማተኮር ይሻላል። ደራሲዉ በዚህ ጽሑፍ ማስተላለፍ የፈለገዉ አጠቃላይ መልዕክት የሚከተለዉን ነዉ። ጫልቱ የሚል የኦሮሞ ስም ይዛ አዲስ አበባ ዉስጥ መኖር ስለማትችል ስሟን ለመቀየር መገደዷ፣ በግድ አማርኛ እንድትናገር መገደዷ፣ በንቅሳቷ እንድታፍር መደረጓ፣ ያደገችበትና ትኮራበት የነበረዉ ባሕል አዲስ አበባ ዉስጥ ዋጋ አለመሰጠቱና ከዚያም በላይ መንቋሸሹ፣ ወደትዉልድ ቀየዋ ስትመለስ ስሟን በመቀየሯና ኦሮምኛ ረሳሁ በማለቷ መሳቂያ እንደሆነች … ይተርክና በመጨረሻም እንደሄለን መሆንም ሆነ ወቀደድሞ ጫልቱ ማንነቷ መመለስ ባለመቻሏ ለሞት እንደተዳረገች ይተርካል። ታዲያ ለዚህች ልጅ ሞት ተጠያቂዉ የአማራ ብሔር ወይስ ብሔረሰቦች በማንነታቸዉ እንዳይኮሩ "የአማራ ገዥ መደቦች" የሚሏቸዉ የፈጠሩት አስተሳሰብ ወይም ባሕል?

ጫልቱ ስሟን የቀየረችዉም ሆነ ኦሮምኛ እንዳትናገር ተጽዕኖ ያሳደረችባት የገዛ አክስቷ እንጂ ሌላ የዉጭ አካል አይደለም። የምትኮራበትን ባሕል ያጣጣለችባትና ከጥንቅላ ጋር ያያዘችዉም ይህችዉ አክስቷ ነች። በንቅሳቷም ማፈር የጀመረችዉ ገና ከቤት ነዉ። እንደዉም አባቷ እንደዚያ በማድረጉ አክስቷ እንደበደለኛ ቆጥሯዋለች።

ቋንቋ መግባቢያ ነዉ። አማርኛ ብሔራዊ ቋንቋ ነዉ። ስለሆነም ኦሮምኛ እንዳለ ሆኖ አማርኛ ማወቅ አስፈላጊነቱ አጠያያቂ አይደለም። ቀደም ሲል በአዲስ አበባ ዉስጥም ሆነ በሌሎች አካባቢዎች በአፍ መፍቻ ቋንቋ መጠቀም የሚከለከልበት ሥርዓት ወይም አካባቢያዊ ተጽዕኖ መኖሩን አላዉቅም። በደርግ ጊዜ ነበርኩ። እንደዉም ደርግ ሲወድቅ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ተማሪ ነበርኩ። በዚያ ሥርዓት ወቅት ሰዎች በኦሮምኛ፣ በትግሪኛ፣ በጉራጊኛ … ወዘተ ሳያፍሩ ዘና ብለዉ ሲያወሩ አስታዉሳለሁ። ከስድስተኛ እስከስምንተኛ ክፍል ድረስ የቀድሞ አምሃ ደስታ እና የአሁኑ እንጦጦ አምባ መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ስለተማርኩ የአካባቢዉ ሰዎች ሳይሸማቀቁ በዶርዝኛ ሲያወሩ እንሰማ ነበር። በወቅቱ የሚያሾፍ ሰዉ አጋጥሞኝ አያዉቅም።

መጠሪያ ስሞች እንደአካባቢዉ ባሕልና ልማድ ይለያያሉ። አንዱ አካባቢ የሚወደዱ ስሞች ሌላ አካባቢ እምብዛም ጥቅም ላይ ላይዉሉ ይችላል። እንዲሁም ከጊዜ ጋር እየቀሩ የሄዱ ስሞችም ይኖራሉ። ከተማ ዉስጥ የማይዘወተሩ ስሞች ሲያጋጥሙ ተማሪዎች ለመቀለድ ወይም ለማብሸቅ ሙከራ ሲያደርጉ ይታያል። ይህ ግን ካለመብሰል የመነጨ ነዉ። የሆነዉ ሆኖ ከብሔር ጋር የተገናኘ አይመስለኝም። ምክንያቱም በርካታ የገጠሩ ኅብረተሰብ የሚጠቀምባቸዉ የአማራ ስሞች በከተማ ተማሪዎች ዘንድ ለማብሸቂያነት ወይም ለተረብ ምንጭ ሆነዉ ሲያገለግሉ እናዉቃለን። እዚህ ጽሑፍ ላይ ማስፈር አልፈልግም እንጂ እንደዚያ ዓይነት በርካታ ስሞችን አስታዉሳለሁ። ወደአሜሪካ ልመጣ አካባቢ አንድ ጓደኛዬ የነገረኝን ታሪክ ግን መጥቀስ እችላለሁ።

የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች ናቸዉ። በአዲስ ዓመት ትምህርት ቤት ሲከፈት እንደተለመደዉ ተማሪዎቹ እርስ በርስ መተዋወቅ ይጀምራሉ። የአንደኛዉ ልጅ ስም ከሌሎቹ ለየት ይል ነበር። በርግጥ በአማራዉ ኅብረተሰብ ዘንድ በስፋት የሚታወቅና ጥሩ ትርጓሜ ያለዉ ስም ነዉ። ምናልባት በአሁኑ ወቅት "ቆየት" ካሉ ስሞች መካከል ሊመደብ ይችል ይሆናል። እናም በሚቀጥለዉ ቀን ሲገናኙ ተማሪዎቹ ምን አሉት መሰላችሁ? በአንድ ድምፅ "የትልቅ ሰዉ ስም" በማለት አበሸቁት። ይህ ልጅ ምን ያህል ሊሸማቀቅ እንደሚችል ገምቱት? የዚህ ልጅ ስም እንዳጋጣሚ የኦሮሞ ማኅበረሰብ የሚጠቀምበት ስም ቢሆን ኖሮ በእነተስፋዬ ገብረአብ ዘንድ ሌላ ትርጓሜ ተሰጥቶት እንዴት ሊራገብ እንደሚችል መገመት ይቻላል። ይህም ብቻ አይደለም። ወላጆቻቸዉ ባወጡላቸዉ ስም በማፈር ወይም በመሳቀቅ ወይም ከነሱ ጋር አብሮ የሚሄድ ስለማይመስላቸዉ ሌላ ስም እስከማዉጣት የደረሱ በርካታ ሰዎችን  በቤተሰብ ደረጃ እናዉቃለን።

ንቅሳት በኢትዮጵያ ዉስጥ በስፋት ይታወቃል። በርግጥ በአሁኑ ሰዓት በተለያየ ምክንያት እየቀነሰ የመጣ ይመስላል። የሆነዉ ሆኖ በተለይም በአማራ፣ በትግራይና በኦሮምያ ገጠራማ አካባቢዎች ራስን ለማስዋብ ግንባር፣ ጉንጭና አንገት ላይ ንቅሳት ማየት የተለመደ ነበር። የከተማ ባሕል ስላልሆነ ልክ እንደስሙ በትምህርት ቤት አካባቢ ልጆች ሊቀልዱበት ይችላሉ። እነዚያን ልጆች ሊያሸማቅቅ ስለሚችል አግባብ አይደለም። ሆኖም ግን ልጆቹ መሳቃቸዉን እንጂ በሌላዉ ላይ ሊደርስበት የሚችለዉን የሞራል ዉድቀት ስለማይረዱ ማንም ከዚያ ሊተርፍ አይችልም። የእንደዚያ ዓይነት ልጆችን ሞራል ለመጠበቅና እንዳይሸማቀቁ ለማድረግ የቤተሰብ፣ የአካባቢ ማኅበረሰብ እና በዋንኛነት የመምህራን አስተዋጽዖ ወሳኝ ይመስለኛል። በዚህ ረገድ ደራሲዉ የጠቀሳቸዉ መምህር ጽጌ በጫልቱ ንቅሳት ተማሪዎች እንዳያሾፉባት በመገሰጽና እሷም በማንነቷ እንድትኮራ ያደረጉት እገዛ በመልካምነት ሊጠቀስ የሚገባ ነዉ። እንዲሁም የገዛ አክስቷ ከጅምሩ ሊያፈርሱት የተነሱትን ማንነቷን ለመጠገን ሙከራ ሲያደርጉ ከነበሩት መካከልም የአክስቷ ባል ተጠቃሽ ናቸዉ። እነዚህ ሁለቱም ግለሰቦች ደራሲዉ በአማራነት የሣላቸዉ ናቸዉ። ዓላማዉ ማጥላላት ሆኖ ሳለ ለምን እንደዚህ ዓይነት አዎንታዊ ሚና እንዲጫወቱ እንዳደረጋቸዉ አልገባኝም። ምናልባት ሐቅ ተናንቆት ይሆን? ለማንኛዉም በማናቸዉም ኅብረተሰብ ላይ ሊደርስ የሚችለዉን

አጋጣሚ ጫልቱ ላይ በኦሮሞነቷ እንደደረሰባት በማስመስል ለማቅረብ የሞከረዉ ፍጹም አግባብ ያልሆነና ከእዉነታዉ የራቀ መሆኑን ለመረዳት ይቻላል። እስኪ አስቡት። እንደነዚህ ዓይነት ጽሑፎችን አዲሱ ትዉልድ በሚያነቡበት ጊዜ ምን ስሜት ሊያድርባቸዉ ይችላል?

ከዚሁ መጽሐፍ ሳንወጣ ከገጽ 216 ጀምሮ "ናደዉ እና ታሪኩ" በሚል ርዕስ የቀረበ ጽሑፍ እናገኛለን። ይህ ጽሑፍ የሚያወሳዉ ስለናደዉ ጦርና ስለጄኔራል ታሪኩ አገዳደል ነዉ። የእኔን ትኩረት የሳበዉ በገጽ 220 ላይ የተጠቀሰዉ አባባል ነዉ። ይኸዉም " ... መንግሥቱ (የቀድሞዉን ፕሬዚዳንት መንግሥቱ ኃ/ማርያምን ለማለት ነዉ) ከደርዘን ንግግሩ መካከል ጄኔራል ታሪኩን ለመግደል ያበቃዉ ምክንያት ማቅረብ አልቻለም። ለአብነት የነጋዴነት ዝንባሌ ነበረዉ በማለት ያጣጥለዋል። ይህንንም ከጉራጌነቱ ጋር እንዲያያዝለት ፈለገ ... አስረጂ ሲያቀርብ ... 'ሰላሳ ሳንቲም የሚሸጠዉን ለስላሳ መጠጥ ለሠራዊቱ በአንድ ብር እየሸጠ፤ ከአንድ ለስላሳ ሰባ ሳንቲም አትርፎ ወደኪሱ ይከት ነበር' ይለናል ..." በሚል ተቀምጧል። ፕሬዚዳንቱ ስለብሔር አላነሱም። ሁላችንም እንደምናዉቀዉ እንደዚያ አስበዉ ቢሆን ኖሮ ሳያሽሞኖሙኑ ፊትለፊት ይናገሩት ነበር። ደግሞም ነጋዴነት ከጉራጌነት ጋር የሚያያዝበት ምክንያት አይታየኝም። ለማንኛዉም ግለሰቡ ሰዎች ባላሰቡት መንገድ ሁሉንም ነገር እንዴት ወደ ብሔር ጠምዝዞ የመዉሰድ አባዜ እንዳደረበት በግልጽ ያሳያል።

### 3) <u>*ቃለ መጠይቅ*</u>

ተስፋዬ ገብረአብ እ.ኤ.አ. ከኦሮሞ ሚዲያ ኔትወርክ ጋር በጋዜጠኛ በፍቃዱ ሞረዳ በኩል ቃለ መጠየቅ አድርጎ ነበር (እ.ኤ.አ. በNov. 1, 2014 ይመስለኛል)። ቃለ መጠይቁ በርካታ ጉዳዮችን የዳሰሰ ሲሆን የእኔን ትኩረት የሳበዉ ግን ስለዕዉቁ ደራሲ በዓሉ ግርማ የጠቀሰዉ ክፍል ነዉ። " ... በዓሉ ግርማ በረቀቀ ዘዴ የኦሮሞን ጥያቄ ያነሣ ነበር" ይልና በመቀጠልም "በኢትዮጵያ ደራስያን ታሪክ ዉስጥ የኦሮሞን ጥያቄ በቅድሚያ ያነሳዉ በዓሉ ግርማ ነዉ ... ቀጥሎ ኦሮማይ ላይ አነሣ። የኦሮሞ ሕዝብ ትግል ላይ እንዳለ ፍንጭ ሰጠ። ታደሰ ቆሪቾ የሚባል ሰዉ አመጣ። የሉሊት ታደሰን አባት አመጣዉ ... " በማለት ያጠናክረዋል።

የበዓሉ ግርማ የመጀመሪያ ድርሰት በሆነዉ "ከአድማስ ባሻገር" ላይ ሉሊት ታደሰ የምትባል ገጸ ባሕሪ አለች። ቀደምት ስሟ ጫልቱ ቶሎሳ ነበር። ስሟን የቀየረችዉ ራሷን እንደጠይም ጣዖት ስለምትመስል "ጫልቱ" የሚለዉ ስያሜ ለዚያ የሚስማማ ባለመሆኑ እንደሆነ እዚያዉ መጽሐፍ ላይ ተጠቅሷል። ተስፋዬ ገብረአብ ግን በማንነቷ በማፈሯ ራሷን ለመደበቅ ስትል ያደረገችዉ ለማስመሰል ሞክሯል። ሌላዉ የሚገርመዉ ይህንን ታሪክ ከ"ኦሮማይ" መጽሐፍ ጋር ለማያያዝ መሞከሩ ነዉ። እንደሚታወቀዉ "ኦሮማይ" የበዓሉ ግርማ የመጨረሻ ድርሰትና ሕይወቱን ያጣበት መጽሐፍ ነዉ። እዚህ መጽሐፍ ላይ ሻለቃ ታደሰ ቆሪቾ የሚባል ሰዉ ተጠቅሷል። የአርሚ አቬሽን ትራፊክና ስምሪት ኃላፊ ነበር። ይህ ሻለቃ በስዉር ለሻዕቢያ ይሠራ ከነበረና ዕቁበ ሲላ ከሚባል መካኒክ ጋር በመተባበር ወደ አዲስ አበባ መሣሪያ ሲልክ ነበር። እንዲሁም "የኦሮማይን ተልዕኮ" በቅጥረኛነት ከሚያስፈጽሙ ሰዎች ዝርዝር ዉስጥም ነበር። ለማገናዘብ እንዲረዳ ሻለቃዉ የተጠቀሰበት ክፍል ገጽ 32 -33፣ 182- 184፣ 242 – 244 እና 367 ናቸዉ።

ዕቁበ ሲላ በትዉልድ ኤርትራዊ ነዉ። የሻዕቢያን ዓላማ በመደገፍ በስዉር ቢተባበር አያስደንቅም። በርካታ የትግራይ ሰዎችም በመንግሥት ሥራ ላይ ሆነዉ በስዉር መረጃ በማቀበልና ሌሎች አደገኛ ተግባራት በመፈጸም ለወያኔ ሲረዱ እንደነበር ዛሬ ያደባባይ ምስጢር ሆኗል። እነዚህ ሰዎች "የዉስጥ አርበኛ" እየተባሉ ሊሞካሹም ይችላል። ሻለቃ ታደሰ ቆሪቾ ግን ሲተባበራቸዉ የነበረዉ ዓላማቸዉን ደግፎት አልነበረም። ዕድሜዉ ለጡረታ ቢደርስም ምንም ቅሪት አለመያዙ ይሰማዉ ስለነበር ለገንዘብ ጥቅም ሲል ብቻ እንደነበር ከገጽ 33 እና 244 መረዳት ይቻላል።

ለጊዜዉ ብሔሩን ትተን ሻለቃ ታደሰ ቆሪቾ ኢትዮጵያዊ ነዉ። በመሆኑም የሻዕብያን የመገንጠል ዓላማ ከልቡ አምኖበት ሊደግፍና ሊተባበር የሚችልበት ምክንያት አይኖርም። በዚያ ላይ ለአገሩ አንድነትና ዳር ድንበር መከበር ሕይወቱን ለመሰዋዕት ቃለ መሐላ የገባ ወታደር ነዉ። በዚህም የተነሣ የፈጸመዉ ድርጊት ከአንድ ወታደር የማይጠበቅ ከፍተኛ የአገር ክሕደት ወንጀል ነዉ።

ተስፋዬ ገብረአብ ግን በዓሉ ግርማ የኦሮሞ ሕዝብ ትግል ላይ እንዳለ ለማሳየት የሉሊት ታደሰን አባት "ኦሮማይ" ላይ በሻለቃ ታደሰ ቆሪቾ መስሎ እንዳቀረበዉ በድፍረት ይናገራል። በመጀመሪያ ደረጃ በየትኛዉም የተለጠጠ አተረጓጎም ብንሄድ የሉሊት አባትና ሻለቃ ታደሰ ቆሪቾን የሚያስተሳስራቸዉ አንዳችም ነገር ማግኘት አንችልም። በዚያ ላይ ከላይ እንደተገለጸዉ "ታደሰ" የሚለዉ ስም የሉሊት ፈጠራ እንጂ የእዉነተኛ የአባቷ ስም አይደለም። ሻለቃ ታደሰ ቆሪቾ ደግሞ አባትና እናቱ ያወጡለትን ስም ስለመቀየሩ የተወሳ ነገር የለም። በመሆኑም ደራሲ በዓሉ ግርማ ባላሰበዉ መንገድ ለራሱ ዓላማ እንዲስማማ ሲል ብቻ እንደዚያ ዓይነት ትልቅ ድምዳሜ ላይ መድረሱ የሚያሳዝንና የሚያሳፍር ነዉ።

በሁለተኛ ደረጃ ሻለቃ ታደሰ ቆሪቾ የሉሊት አባት ነዉ ብለን ብንቀበል እንኳን ከተስፋዬ ገብረአብ መሠሪ መልዕክት ጋር የሚሄድ አይደለም። የኦሮሞ ሕዝብ ኩሩና አገሩን የሚወድ ነዉ። ከጥንት ጀምሮ የአገሩን አንድነትና ዳር ድንበር ለማስከበር ሲዋደቁ የነበሩ በርካታ ጀግኖችን ያፈራ ሕዝብ ነዉ። በኢትዮጵያና በሻዕብያ መካከል በተደረገዉ ጦርነት እንኳን በርካታ አንቱ የተባሉ የኦሮሞ ብሔር የሆኑ ጄኔራሎች ተሳትፈዉበታል። ለምሳሌ ጄኔራል ደምሴ ቡልቶ፣ ጄኔራል ካሳዬ ጨመዳ፣

ጄኔራል ረጋሳ ጅማ ... ወዘተ እያሉ መሄድ ይቻላል። በርግጥ እንደማንኛዉም ሕዝብ የኦሮሞ ሕዝብም መንግሥትንና አገዛዝን በመቃወም እንቅስቃሴ ዉስጥ በስፋት ተሳትፏል። በቅርቡም በአገራችን የታየዉ የሚያረጋግጠዉ ይህንኑ ነዉ። የሆነዉ ሆኖ የኦሮሞ ሕዝብ ትግል ለተራ የገንዘብ ጥቅም ሲል አገሩን ክዶ ለሻዕብያ የጦር መሣሪያ ሲያሻግር ከነበረዉ ሻለቃ ታደሰ ቆሪቾ ጋር ለማመሳሰል መሞከር የኦሮሞን ሕዝብ የሚያዋርድ እንጂ የሚያኮፍስ አይሆንም። የደራሲ በዓሉ ግርማ ክብርንም የሚነካ ነዉ።

በዓሉ ግርማ በእናቱ ኦሮሞ እንዲሁም በአባቱ ሕንዳዊ ነዉ። ይህ ዕንቁ ደራሲ ከኦድማስ ባሻገር፣ የሕሊና ደወል፣ የቀይ ኮከብ ጥሪ፣ ደራሲዉ፣ ሀዲስ እና ኦሮማይ የተሰኙ ስድስት መጽሐፍትን ለንባብ አብቅቷል። በአጻጻፍ ስልቱ ብቻ ሳይሆን ጽሑፎቹ በሚይዟቸዉ ጥልቅ መልዕክቶች ጭምር ለማንበብ የታደለ ሁሉ የሚመሰክረዉ ነዉ። ከነዚህ መጻሕፍት ዉስጥ የኦሮሞን ሕዝብ ነጥሎ ወገንተኛነት ያሳየበት አንድም ቦታ የለም። ተጀምሮ እስከሚጨረስ ድረስ ሲጽፍ የኖረዉ እንዳንድ ኢትዮጵያዊ ነዉ። መጨረሻም ኦሮማይን የጻፈዉ ለእናት አገሩ ካለዉ ፍቅርና ተቆርቋሪነት ነዉ። እኔ በበኩሌ ከእሱ መጽሐፍ ዉስጥ ኦሮሞ መሆኑን የጠቆመበትን/ያንጸባረቀበትን ክፍል አይቼ አላዉቅም። ተስፋዬ ገብረአብ ግን የመሠሪ ዓላማዉ ኢጋር አድርጎ ለማቅረብ ሲታክት ይታያል። ይህ በፍጹም ተገቢ ያልሆነና የጽሑፉንም ዓላማ የሚያዛባ ነዉ። ሕይወቱንም ያጣበትንም ትልቅ መስዋዕት ጠበብ ተደርጎ እንዲታይ የሚያደርግ ነዉ። እንደጀመረዉ ራሱን ችሎ ቢሄድ ይሻል ነበር። በነገራችን ላይ በዚያ ቃለ መጠይቅ ወቅት ሎሬት ጸጋየ ገብረመድኅንም የኦሮሞ ብሔርተኝነት ስሜት እንዳለዉ ለማሳየት በግጥሙ ዉስጥ የተጠቀመባቸዉን የኦሮምኛ ስያሜዎች በማጣቀስ ለማያያዝ ሙከራ አድርጓል። በሥነ ግጥም ላይ ጎበዝ ባልሆንም የእሱን ግጥሞች ለማየት እንደሞከርኩት ኢትዮጵያን በአራቱም ማዕዘን ከጫፍ እስከጫፍ የሚነካ ሆኖ ነዉ ያገኘሁት። አንድም ቦታ የኦሮሞ ብሔርተኝነትን የሚያሳይ ነገር አላየሁም። ይህ ማለት ኦሮሞ አይደለም ማለት አይደለም። ወይም በኦሮሞነቱ አይኮራም ለማለት አይደለም። በጽሑፉ የምናዉቀዉ ግን በኢትዮጵያዊነቱ ብቻ ነዉ።

ለማጠቃለል ያህል አገራችን በአሁኑ ሰዓት ያለችዉ ማነቆ ላይ ነዉ። ሥልጣን ላይ ያለዉ መንግሥት የራሱን ድብቅ አጀንዳ (የአንድ ብሔር የፖለቲካና የኢኮኖሚ የበላይነት ማስፈን) ለማራመድ ሲል በሕዝብ መካከል አለመተማመን እንዲሰፍን አንዱን ብሔር ጨቋኝ ሌላዉን ደግሞ ተጨቋኝ በማድረግ ከፋፍሎ የመግዛት መርሑን ተግባራዊ እያደረገዉ ነዉ። በዚህ እየተጠቁሙ ያሉ ጥቂት ግለሰቦች ናቸዉ። ቀሪዉ የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን በድኅነት፣ በፍትሕና በመልካም አስተዳደር እጦት እየተሰቃየ ነዉ።

ተቀናቃኞቹን ለማጥፋትና ለማሰቃየት ሲል እንደ ጸረ-ሽብር አዋጅ የመሳሰሉ ሕጎችን በማዉጣት በየቀኑ በርካታ ዜጎች ለእስራት እየተዳረጉ ነዉ። ግድያዉና አፈናዉም በስፋት ቀጥሏል። ትናንትና በኦሮምያ፣ በጎንደርና በባህር ዳር ላይ የደረሰዉን ፍጅት የምንረሳዉ አይደለም። በተለይም የእሬቻ በዓል ሲከበር በሰዓታት ዉስጥ ከአምስት መቶ በላይ የሞቱት ዜጎቻችን ደም በከንቱ ፈሶ መቅረት የለበትም።

ዛሬ እየሆነ ባለዉ ነገር ላይ ማተኮርና መታገል ሲገባን ወደኋላ ታሪክ እየጠቀስን የምንናቆርበት ጊዜ አይደለም። በአንድ ወቅት ጥፋት ተሠርቶም ከሆነ ወደፊት እንዳይደገም ለመማሪያነት እንዲያገለግል ከማዉሳት ባሻገር የልዩነት ምንጭ ሆኖ የሚያናቁር ሊሆን አይገባም። ልዩነታችንን በማጥበብ አንድ ሆነን በአንድ ላይ በመነሣት ትግል ማካሄድ ግድ የሚልበት ጊዜ ላይ ነን። ወደድንም ጠላንም ሁላችንም የምንመኘዉ በጎ ለዉጥ ሊመጣ የሚችለዉ አንድ ላይ ሆነን መታገል ስንችል ብቻ ነዉ። የተናጠል ትግል የትም አያደርሰንም። ዉጤቱን እያየነዉ ነዉ። ወያኔ/ኢ.ሕ.አ.ዲ.ግ. ሥልጣን የያዘበትን ሃያ ስድስተኛ ዓመቱን እያከበረ ነዉ። ወደፊትስ ምን ያህል ጊዜ ይቆያል? የምናዉቀዉ ነገር የለም።

ቸር ይግጠመን

የዚህን ጽሑፍ አቅራቢ ለማግኘት ለምትፈልጉ፡- mekonnen_ashagre@yahoo.com